# የአውራምባ ማህበረሰብ አመሰራረትና የሚከተለው ፍልስፍና ክፍል አንድ

**(ከጎንደር መልስ - የጉዞ ማስታወሻ)፣** ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ በአ.አ.ዩ የህግና የፌዴራሊዝም መምህር

1. *መግቢያ:-*

ድህነት በተንሠራፋባት፣ ኋላቀር አስተሳሰብ ሥር በሰደደባት፣ የሃይማኖትና የባሕል ተጽእኖ ጠንክሮ በሚታይባት ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስና በመሰረቱ የተለየ አስተሳሰብ በተለይም በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ነውር የሚቆጠር ፍልስፍና ይዞ ብቅ ማለት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በሌላ አባባል ያረጀና ያፈጀውን እሣቤ ሽሮ ለለውጥ የሚበጅ ተራማጅ የሆነ አስተሣሰብ ማመንጨት፣ መቀበልና መተግበር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም ብቻ ሣይሆን በአንድ አካባቢ መንጭቶ ሲቀርብ ለማመንና ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎች ቢያስገድዱት እንኳ እጅግ ፈታኝና አዝጋሚ መሆኑ አይቀርም፡፡

ይሁን እንጅ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኘው የደቡብ ጐንደር አስተዳደር ዞን ፎገራ ወረዳ ውስጥ የሚገኝና አሁን ካለው ሕብረተሰብ አመለካከት አንጻር ሲታይ በእጅጉ ያፈነገጠ ወይም ወጣ ያለ የሚመስል ነገር ግን እጅግ ተራማጅና ጠቃሚ የሆነ አስተሳሰብና ጠንካራ የስራ ባህል በመያዝ ራሱን አቅንቶና ለመስዋዕትነትም አዘጋጅቶ ኋላ ቀር አመላካከቶችንና ጎታች የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችን ታግሎ በማሸነፍ ከጠፍር የጠነከረውን ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ጫና በጽናት የመከተና ድህነትን ተረት ለማድረግ ዘላቂ ሕይወቱን በሥራና በሥራ ብቻ ለመለወጥ ቀኑ አልበቃው ብሎት መሽቶ እስኪነጋ ድረስ ሲባትል የሚኖር፣ መተሳሰሪያ ገመዱን ፍቅርና ዘላቂ ህይወቱንም ስራ ያደረገ ማህበረሰብ ከተመሰረተ 40 አመት ሞላው ቢባል ለአንዳንዶቻችን በእርግጥም ለማመን ይከብድ ይሆናል፡፡

ይህ ማህበረሰብ አውራምባ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጠንካራ የስራ ባህሉና በመልካም ስነምግባሩ ታዋቂነትንና ዝናን እያተረፈ የመጣ፣ ታታሪነትን መለያቸው ያደረጉ አባላት የተሰበሰቡበት፣ የመልካም አስተዳደርና የጠንካራ የስራ ባህል ባለቤት እንዲሁም የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት መሆን በመቻሉ የቱሪስቶችንና የጋዜጠኞቹን ቀልብ በቀላሉ መሳብ የቻለ ማህበራሰብ ለመሆንም በቅቷል፡፡ የዚህ አጭር ጽሁፍ ዋነኛ አላማም የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ መልካም አስተሳሰብና በጎ ምግባር እንዲሁም ጠንካራ የስራ ባህል በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ማበረታታት ነው፡፡

2. **የማህበረሰቡ አነሣስ /አመሠራረት/:-**

የአውራምባ ማህበረሰብ እንዴትና መቼ እንደተመሠረተ ለማህበረሰቡ ልደትና ዘላቂ ሕልውና መሠረት የሆነው ፍልስፍና (እምነት) እንደምንና ከየት ሊመነጭ እንደቻለ ለማወቅ የማህበረሰቡ መሥራችና መሪ የሆኑትን አቶ ዙምራ ኑሩን በአካል አግኝቶ ስለሁኔታው ማንጋገርን የግድ ይላል፡፡ በመሆኑም አቶ ዙምራ የማህበረሰቡን አነሣስ አስመልክተው ሲጠየቁ በአጭሩ የሚከተለውን መልስ በመስጠት ሁኔታውን ያብራራሉ፡፡ ወላጆቼ ገበሬዎች ነበሩ የሚተዳደሩትም በእርሻ ሥራና ከብት በማርባት ነበር፣ ኑሮአቸውም ድካም የሞላበት፣ ችግር የወረሰውና ከእጅ ወደ አፍ ያልዘለለ ነበር፡፡ ገና የሁለትና የሦስት አመት ልጅ ሣለሁ ከታዘብኳቸውና በወቅቱ ስሜቴን በእጅጉ ካቆሰሉት ሁኔታዎች መካከል አንዱ የጾታ የበላይነትና የበታችነት ሁኔታ ነግሶ ማዬቴ ነበር፡፡ ሁለቱም ወላጆቼ ቀኑን ሙሉ አብረው በሥራ ተጠምደው ሲባክኑ ውለው አመሻሽ ላይ ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡

ይሁን እንጅ የአባቴ ሥራ እዛው ማሳ ላይ የቀረ ይመስል መጥቶ ቤቱ አረፍ ሲል የእናቴ ግን ቢያንስ እስከ ምሽቱ አምስትና ስድስት ስአት ድረስ ይቀጥላል፡፡ በመሆኑም እናቴ ነግቶ እስኪመሽ፣ መሽቶ እስኪነጋ ጭምር የምትለፋው ልፋት የሁሉም ሴቶች እጣ ፈንታ መሆኑን በልጅነት አእምሮየ እየተገነዘብሁ መጣሁ ይላሉ አቶ ዙምራ ኑሩ የልጅነት ትውሰታቸውን መለስ ብለው በመቃኘት፡፡ ቀጥለውም ችግሯን ያቃለልሁ መስሎኝ እናቴን በሥራ ላግዛት ሞከርኩ፣ ሆኖም ገና ሕጻን በመሆኔ የሚቻለኝ አልሆነም፡፡ ተወልጄ ያደግሁበትን አካባቢ ሕብረተሰብ አኗኗር ልብ ብዬ ስመለከተው ደግሞ ማህበራዊና ባህላዊ ሕይወቱ በሌላም ችግር የተተበተበ ሆኖ አገኘሁት፡፡ ሥርቆት፣ ጸብ፣ ውሸት፣ እርስ በርስ መበዳደልና ያለአግባብ መጠቃቀም በግልጽ ሰፍኖ ይታያል ብቻ ሣይሆን አንዱ የሌላውን መብት በግልጽ ይጋፋል፣ ለግል ጥቅም ማጋበስና

ለስልጣን ሲባል ግጭት ይፈጥራል፣ በመሆኑም ፍቅር፣ መከባበር፣ መቻቻልና የመሳሰሉት የሕብረተሰቡ መልካም እሴቶች ብዙም ቦታ ሲሰጣቸው አይስተዋልም፡፡

በዚያ ላይ የከፋ ድህነት አለ፣ ከጥገኝነትና ኋላቀርነት ነጻ አልወጣንም፣ ለህጻናት መብትም ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ አይደረግም ብቻ ሳይሆን በጉብዝና ዘመናቸው ለሀገራቸውና ለወገናቸው ኩራት የነበሩ አረጋዊያንና አቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎች ውለታ ተዘንግቶ አስታዋሽ ማጣት እጣፈንታቸው ሆኖ አገኘሁት፡፡ እነዚህና መሰል አሉታዊ ውጤት የሚያስከትሉ አድራጐቶችና እሣቤዎች ለምን ከህብረተሰቡ መካከል አይወገዱም? እስከመቼስ ነው ከማህበረሰባችን ጋር እንዲህ ተጣብቀው የሚቆዩት? ብየ ከመጠየቅ ጀምሮ ችግሮቹን በዘላቂነት ሊያስወግድ የሚችል መፍትኄ ለማግኘትም በልጅነት አዕምሮየ ማሰላሰል ጀመርሁ በማለት ባለታሪኩ አቶ ዙምራ ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከነዚህ አሉታዊ አስተሣሰቦች ነጻ የወጣ፣ በፍቅርና በእኩልነት የሚያምን እርስ በርሱ የሚተሣሰብና የሚረዳዳ፣ በሥራና ሰርቶ በማደግ ብቻ የሚተማመንና ለዘላቂ ሕይወቱ መለወጥ ጠንክሮ ለመሥራት የሚተጋ ሕብረተሰብን ማዬት ተመኘሁ በማለት የመጀመሪያ ህልማቸውን በአጭሩ ይተርካሉ፡፡

ይህን ምኞታቸውን እውን ለማድረግና አዲሱን አስተሳሰባቸውን የሚጋራ ሰው ለማግኘትም ቆላ መውረድ፣ ደጋ መውጣት፣ እንዲያም ሲል ከማህበረሰቡ ጋር መጋጨትና መገለል ነበረባቸው በወቅቱ እንደ አፈንጋጭ አሊያም እንደ ዕብድ ይቆጠሩ ነበርና፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን እድሜያቸው ገና አሥራ ሶስት ዓመትን እንኳ አልዘለለም ነበር፡፡ ድካምና ልፋቱ ሳይበግራቸው በዚህ የጨቅላነት ዕድሜያቸው ወሎን፣ ጐንደርንና ጐጃምን አካለሉ፡፡ ለአሥራ ሰባት ዓመታት መውጣት መውረዱ ቀጥሎ የኋላ ኋላ ልፋትና ድካማቸው መና ባለመቅረቱ ፎገራ ወረዳ ውስጥ ጥቂት ተከታዮችን ከጐናቸው ማሰለፍ ቻሉ፡፡ እናም ዙምራ የተመኙትና የናፈቁት ብሎም በልጅነት እድሜያቸው ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉለት አስተሣሰብ በ1964 ዓ.ም እውን ሆኖ መተሳሰሪያውን ፍቅር ህይወቱን ሥራ ያደረገ ማህበረሰብ በይፋ ተመሠረተ፡፡ ይህንንም ማህበረሰብ አውራምባ ብለው ሰየሙት፣ ይኸውና በአሁኑ ወቅት ማህበረሰቡ የተመሰረተበትን 40ኛ አመት ከአንድ አመት በፊት በደመቀ ሁኔታ አክብሮ፣ ዳጋፊዎቹን አበራክቶና አርአያነቱንም አጠናክሮ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአለም ማህበረሰብ ዘንድም አስተሳሰቡ ተቀባይነት እያገኘ መጥቶ የብዙዎቹን ቀለብ ለመሳብ በቅቷል፡፡

## 3. የማህበረሰቡ የሥራ ባህል፣-

የአውራምባ ማህበረሰብ አባላት የስራ ባህል፣ የሚመሩበት የአኗኗር ዘይቤና የሚከተሉት ፍልስፍና ከሌላው ሕብረተሰብ በብዙ መልኩ እንዲለዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ማህበረሰቡ በአስተሣሰብና በእምነት ፍጹም ለየት ያለ በመሆኑ እምነቱን ፍቅር፣ ሐማኖቱን ደግሞ ሥራ ያደረገ መሆኑ ብቻ ሣይሆን ይህ ሥራ የሴት ይህኛው ደግሞ የወንድ የሚባል የሥራ ክፍፍልንም ሆነ ልዩነትን አይቀበልም፡፡ ሴቶች በሬዎችን ጠምደው ያርሣሉ፣ ሸማ ይሠራሉ፣ በአጠቃላይም በተለምዶ የወንድ ሥራ ተብሎ በሚታወቀው ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉ በእኩል ይሣተፋሉ፣ ወንዶች እንጀራ ይጋግራሉ፣ ወጥ ይሠራሉ፣ ጥጥ ይፈትላሉ ወዘተ. ብቻ ስራን ሳይንቁና ወደ ሌላ ሳይገፉ በኩራት ይሰሩታል እንጅ ሀፍረት ብሎ ነገር አይስተዋልባቸውም አውራምባዎች፡፡

ስለሆነም አውራምባዎች ሥራ ያሉትንና ለህይወታቸው ጠቃሚ ነው ብለው ያመኑበትን ሁሉ ተባብረውና ተከባብረው እንዲሁም ተግባብተው ይሠሩታል፣ የጾታ ልዩነት ሣያግዳቸውና የከባቢው ህብረተሰብ የተሳሳተ አስተሳሰብ እንቅፋትነት ሳይገታቸው ያቀላጥፉታል፡፡ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ከድህነትና ኋላ ቀርነት መላቀቅ የሚቻለው በሥራ እንጅ ቁጭ ብሎ ከሰማይ መና እንዲወርድለት በመጸለይ እንዳልሆነ በጽናት ያምናሉ፡፡ እናም ኑሮአቸውን ለማሻሻልና ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ሌት ተቀን ተግተው ይሠራሉ፣ ለለውጥና ለሥራ ማነቆ የሆኑ ኋላቀር አስተሣሰቦችንና ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጽናት ይታገሏቸዋል እንጅ በጭራሽ ለማስታመም አይሞክሩም ብቻ ሳይሆን ለማደናቅፍ ለሚሞክሩ ስራ ፈቶችና ኋላ ቀሮችም ጊዜና ቦታ መድበው ሀሳባቸውን እንዲያደናቅፉባቸው ዕድል አይሰጧቸውም፡፡

## 4. የማህበረሰቡ እምነት፣-

ለአውራምባዎች ሃይማኖት ማለት ምንድነው? እምነትስ ምን ይመስላል? ብላችሁ ብትጠይቋቸው የሚሰጧችሁ መልስ አጭርና ግልጽ ነው፣ በፍቅርና በሥራ እንተማመናለን፣ ከማለት ጀምሮ በአንድ ፈጣሪ እንደሚያምኑም ያረጋግጡላችኋል፡፡ እንደ አውራምባዎች አስተሳሰብ ከሆነ የክርስትናው መጽሃፍ ቅዱስም ሆነ የእስልምናው ቅዱስ ቁርአን በሐሰት መመስከርን፣ ሥርቆትን፣ ውሸት መናገርን፣ አመንዝራነትን፣ ነፍስ ማጥፋትን ወዘተ. እንደ ቅደም ተከተላቸው ሐጢአት ወይም ሐራም ብለው ፈርጀዋቸዋል፡፡ ለአውራምባዎች

እነዚህን ሀይማኖታዊ ሕግጋት ማክበር /በነዚህ ህግጋት መመራት/ በወሬ ብቻ ሣይሆን በተግባር የእለት ከእለት መመሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ማድረጉ ላይ ነው ቁምነገሩ፡፡

በእርግጥም አውራምባዎች ከላይ የተጠቀሱትን ሕግጋት በሚገባ ሲያከብሯቸውና ሲጠቀሙባቸው ማየት የተለመደ የዕለት ከዕለት ተግባራቸው ስለሆነ አባባላቸው እውነትነት እንዳለው በቀላሉ ለማረጋገጥ አይቸግርም፡፡ በአንድ ድምጽም ሲያጠቃልሉ እግዚአብሄርም አላህ አላህም እግዚአብሄር አይደለምን? የፈጣሪ መጠሪያ ለምን ሁለት እንደሆነ ገና ያልገባንና እስካሁንም ድረስ ያልተመለሰልን ጥያቄ ነው በማለት ጥያቄያችሁን በጥያቄና ፍልስፍናቸውን ቁልጭ አድርጐ በሚያሣይ መልኩ ይመልሱላችኋል፡፡ እንግዲህ አውራምባዎች ለሃይማኖትና እምነት ያላቸው አተያይ እንዲህ የተቆጠበና ማራኪ ሲሆን ይበልጥ ትኩረትና ክብደት ሰጥተው የሚገልጹት ግን ማህበረሰቡ የሚመራበትንና ከጅምሩም የተዋቀረበትን የለውጥ ሀሳብና ማህበራዊ ፍልስፍና ከፍ አድርገው በማንሳት በፍቅርና በሥራ እናምናለን እንተማመናለንም፣ ከዛም አልፎ የአንድ አምላክ መኖርንም እንቀበላለን ሁላችንም የአዳምና የሂዋን ወይም የአደምና የሀዋ ልጆች መሆናችንን አንክድም በማለት ለስራና ለፍቅር ግን ያላቸውን ጽኑ ክብር በድጋሜ ያረጋግጣሉ፡፡

## 5. የአውራምባዎች አስተሳሰብና ፍትህ፡-

በአውራምባ ማህረሰብ ዘንድ ጠብና ድብደባ፣ ስርቆትና ማጭበርበር ቦታ የላቸውም ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ አባላት መካከል ጊዜያዊ አለመግባባት ቢፈጠር እንኳ በማህበረሰቡ ደንብ መሰረት ወዲያውኑ መፍትሄ ያገኛል እንጅ ለአልተፈለገ ግጭት መንስኤ እንዲሆን አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ማለት አንድም በራሳቸው ችግሩን በፈጠሩት ሰዎች መካከል ግልጽ ውይይት በማድረግ አሊያም ሌላ ሶስተኛ ወገን ተጨምሮበት ሰላማዊ በሆነ መንገድ የአለመግባባቱ ዕድሜ እንዲያጥር ይደረጋል፡፡ በዚህም ምክንያት የአውራምባ ማህበረሰብ አባል የሆነ ሰው ላለፉት 40 አመታት ከሌላ ሰው ጋር ተጣላሁ፣ ድንበር ተገፋብኝ፣ ንብረት ተሰረቀብኝ ወይም ተዘረፈብኝ በአጠቃላይም የአስተዳደር በደል ደረሰብኝ ወይም ፍትህ ተጓደለብኝ ብሎ ለፖሊስ ሪፖርት አድርጎ ለፍርድ ቤት ክስ የሚያቀርብበትና በሌላ ሶስተኛ ወገን ፍትህ ለማግኘት ሲል ወርቃማ የሆነውን የስራ ጊዜውን የሚያባክንበት አንዳች ምክንያት እንዳይኖር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

እንደማህበረሰቡ እምነትና አስተሳሰብ ቢሆንማ ኖሮ የፍትህ አካላት ራሳቸው አስፈላጊ ባልሆኑም ነበር፡፡ ይልቁንም ከእነዚህ ተቋማት በላይ ለሰው ልጆች ሁሉ ክብርና ፍቅር መስጠት በመካከላቸው ይፈጠር የነበረውን አለመግባባትና ግጭት በዘላቂነት ከማስቀረቱም በላይ በህብረተሰቡ መካከል አስተማማኝ ሰላም በመፍጠር ሙሉ አቅምን ለልማት፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ፣ ለማህበራዊ ፍትህ መንገስና ለመልካም አስተዳደር መስፈን በአጠቃላይም ለህግ የበላይነት መከበር ማዋል እንደሚቻል ያለፉት አራት አስርት አመታት የህይወት ልምዶቻቸውን ዋቢ በማድረግ በእርግጠኝነት ይናገራሉ፡፡

አዉራምባዎች የአለመግባባትና የግጭት መንስአዎች ናቸው የሚሏቸውን እንደ ስርቆት፣ ሀሰት መናገር (ቅጥፈት)፣ ማጭበርበር፣ ዝሙትና አስካሪ መጠጦችንና አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም የመሳሰሉትን አስነዋሪ የሰው ልጅ ባህሪያትን በማስወገድ በመልካም ስነምግባር መተካት ይቻላል የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው፡፡ በተግባርም እነዚህን ችግሮች በተባበረ ጥረታቸው ከአካባቢያቸው ሙሉ በሙሉ አስወግደው ሰላም የሰፈነበት፣ ፍቅር የነገሰበት፣ እኩልነት የተረጋገጠበት፣ ዕድገትና ብልጽግና በስራና በስራ ብቻ ዕውን ይሆናል የሚል ጠንካራ አቋም የያዘና ለዚህም ተግባራዊነት ሳያሳልስ የሚሰራ ማህበረሰብ በጠንካራ መሰረት ላይ መገንባት ችለዋል፡፡ ቀሪው ነገር ሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ይህን ወርቃማ መርህ የራሱ አድርጎ እንዲተገብረው አጋጣሚዎችን በመጠቀም ጠንክረው መስራት ነው፡፡

## 6. የአውራምባ ማህበረሰብ መሰረታዊ መርሆዎች፡-

አውራምባዎች የዕለት ከዕለት ስራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸውና አጠቃላይ እምነቶቻቸውን የሚያንጸባርቁባቸው የራሳቸው የሆኑና ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የሚያከብሯቸው አጠቃላይ የህይወት መርሆዎች አሏቸው፡፡ ከነዚህ ጠቃሚና በርካታ መርሆዎቻቸው መካከልም የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

6.1 ጾታን መሰረት ያደረገንና አንደኛውን ጾታ ዝቅ አድርጎ ሌላኛውን የሚጠቅም ወይም ከፍ የሚያደርግ ማህበራዊ የስራ ክፍፍልን ማስወገድና ስራ በችሎታ ላይ ብቻ እንዲመሰረት ማድረግ፣

6.2 ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ጎታች ባህላዊና ሀይማኖታዊ አስተሳሰቦችን አስወግዶ ለሰው ልጆች ሁሉ ክብርና ፍቅር በሚሰጥ አዲስና ተራማጅ አስተሳሰብ መተካት፣

6.3 ህጻናትን ስለዕውነት ማስተማር፣ አረጋዊያንንና አቅመ ደካሞችን መርዳትና መንከባከብ እንደ አንድ የማህበረሰቡ የህይወት መርህና ግዴታ አድርጎ መውሰድ፣

6.4 ስርቆትን፣ ሀሰት መናገርን፣ ልመናን፣ ስንፍናን፣ ዝሙትንና ዋልጌነትን በማስወገድ በማህበረሰቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሌላውም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ መልካም ስነምግባርን መገንባት፣

6.5 ጋብቻ በተጋቢዎች ሙሉ ፈቃድ (ፍላጎት) ላይ ብቻ እንዲመሰረት ማድረግና የአንድ ለአንድ ጋብቻን አስፈላጊነት በቀጣይነት ማስተማር እና

6.6 በከፍተኛ ልፋትና ድካም የተገኘ ሀብትን (ጥሪትን) ያለአግባብ የሚያባክን ድግስን በማስቀረት ወርቃማ የሆነውን የስራ ጊዜን የሚሻማ የሰርግም ሆነ የሀዘን ስርአትን ማስወገድ የሚሉት ናቸው፡፡

7. **የአውራምባ ማህበረሰብ አሁን የደረሰበት ደረጃ፣-**

ቀደም ሲል በአንድ ግለሰብ ተነሳሽነት የኋላ ኋላ ደግሞ በጥቂት ግለሰቦች ትብብር የተመሠረተው የአውራምባ ማህበረሰብ በአሁኑ ወቅት ግን ተከታዮቹን እያበራከተ፣ የፍልስፍናውን አድማስ እያሰፋና ፋይዳውንም ለሀገሬው ሕዝብ ብቻ ሣይሆን ለዓለም ማህበረሰብ እያበሰረ፣ ድህነትንና ኋላቀርነትን በተደራጀ መልኩ በመዋጋት ከሰፈሩ ብሎም ከሀገሪቱ ለማስወገድና በተረትነት ብቻ እንዲነገር ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል፡፡ አዲሱ ሚሊኒየም የኢትዮጵያ ሕዳሴ ይሆናል የሚለው የኢትዮጵያ መንግሥት መሪ መፈክርና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱም በሀሳብ ብቻ እንዳይቀር ይልቁንም በተግባር እውን ሆኖ እንዲታይ ግንባር ቀደም ሚናውን ለመጫወትም ቆርጦ መነሣቱን በድርጊት በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ የማህበረሰቡ ፍልስፍና ተራማጅ የሆነው የለውጥ ሀሳብና የሥራ ፍቅር ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎችን የመቀየር ኃይሉ እየተጠናከረ ተቀባይነቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ በቀጣዩ ክፍል በሰፊው የምመለስበት ቢሆንም በየእለቱ የሚጐበኝ፣ በየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ ታሪኩና አስተሳሰቡ የሚተረክለት፣ በአርቲስቶችም ሳይቀር የሚቀነቀንለት ተወዳጅና አርአያነት ያለው ማህበረሰብ ለመሆን በቅቷል፡፡

በሌላ በኩል ሁለገብ የሆነ የልማትና የባሕሪ ለውጥ  ለማምጣት የአውራምባ ማህበረሰብ የልማትና የባሕሪ ግንባታ ማህበርን በማቋቋም በክልሉ ፍትሕ ቢሮ እውቅና አግኝቶ በመንቀሣቀስ ላይ የሚገኝ ሲሆን የማህበረሰቡ አባላት የአመረቱትን ምርት ወደ ገበያ ለማቅረብና የፋብሪካ ውጤቶችን፣ የግብርና ግብአቶችን ጨምሮ ለማህበረሰቡ አባላትና ለአካባቢው አርሶ አደር ጭምር ገዝተው ለማከፋፈል ይችሉ ዘንድ የአውራምባ ማህበረሰብ ሁለገብ የግብርናና የእደ-ጥበባት ማህበርን አቋቋመው በተደራጀ መልኩ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት አንድ አይሱዙ የጭነት መኪና፣ ሁለት የህዝብ ማመላሻ ሚኒባሶችና የበርካታ የምርት መሳሪዎች ባለቤት ሆነው በጥረታቸው ረሀብና ችግርን ደህና ሰንብት ለማለት ችለዋል፡፡

በአጠቃላይም በአሁኑ ወቅት ከ150 በላይ የሚሆኑት የማህበረሰቡ አባወራዎች/እማወራዎች ከ500 በላይ የቤተሰቡ አባላት ጋር በአካባቢው ይገኙ እንጅ በርካታ ደጋፊና ተባባሪ አባል በማፍራታቸው ሽዎች ለመሆን በቅተዋል፡፡ ነገም ሌላ ቀን ነውና በዚህ አያያዛቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ መቶ ሽዎችና ሚሊዮኖች የማይሆኑበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡ ምክንያቱም አስተሳሰባቸው ተራማጅ ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው የሰውን ልጅ አማላይና ፍልስፍናቸው የሁሉንም ማህበረሰብ የምጣኔ ሀብት፣ የማህበራዊ ፍትህና የመልካም አስተዳደር እጦት የሚፈጥረውን አስከፊ ችግር በሒደት የሚያቃልል ስለሆነም ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በእጅጉ እየተጠናከረ መሄዱ አይቀርምና ነው፡፡